# ስለ አዲሱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር

ጌታቸው ረዳ (ኢትዮ ሰማይ አዘጋጅ (Ethio Semay)



እንደተለመደው ወደ ርዕሴ ከመግባቴ በፊት፤ ባለፈው ጽሑፌ ላይ ስለ ሻለቃ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ ወላጅ አባት “ባንዳነት” አንስቼ የማስተካከያ ይቅርታ ጠይቄ እንደነበር ይታወሳል። ሆኖም ሁለት የማውቃቸውና በኢትዮጵያ ታሪክ ጥልቅ እውቀት ያላቸው ወዳጆቼ “ይቅርታ” መጠይቁ ‘ተገቢ’ (ኢምፐሮፐር) እንዳልሆነ፤ ከማስተማመኛ ማስረጃዎች ጋር ስለላኩልኝ፤ የሻለቃው ወላጅ አባት ከነፃነት በኋላ አገራዊ አገልግሎታቸው የሚመሰገን ቢሆንም፤ በጣሊያን ጊዜ ግን የጣሊያን ወታደር ባይሆኑም፤ የጣሊያን ፕሮፓጋንዳ ጽሑፎች (publication) በዋና አዘጋጂነት ጣሊያንን ማገልገላቸው የታወቀ ስለሆነ ‘ማስተካከያህን’ ፈትሽ ስላሉኝ፤ አንስቼዋለሁ።

ለዚህም ሻለቃው የወላጅ አባቱ በእንደ እዚያ ያለ አገልግሎት ለጣሊያን አድረው ሲያገለግሉ እንደበር ቢያውቅም፤አባት ስለሆኑ፤ማንም ሰው የወላጆቹን በጎ ሥራ እንጂ ሸካራ ገመና ለሕዝብ እንደማይገልጥ ግልጽ ነው፡ ሲሉ ትችታቸውን በማጠናከር ለማመን ተገድጃለሁ። ይህ ልክ ወይም ውሸት ብሎ የመከራከር መብቱ ለሻለቃው ትቼአለሁ። በኔ በኩል የታሪክ እውነታን ፍለጋ እንጂ ማንንም ለማሳነስ እንደላሆነ የምታውቁኝ ይመስለኛል። ሻለቃው ዛሬ በሚተራመስበት የታሪክ ጉድፍ ላይ ቆሞ ፤ስለ ኤርትራ የባሕር ባለቤትነት (ጠቅላላም ኤርትራ ምድር እና ሕዝብ) ሽምጡን ገትሮ ለሻዕቢያ እና ለወያኔ ፕሮፓጋንዳ ቆሞ በሕዝብ ፊት ሲከራከርና ‘የዓሰብ ጉዳይ’ ያለቀ ፤ያከተመ ጉዳይ ነው፤የኤርትራን ነፃነት መቀበል ወደድንመ ጠላንም ‘በተባበሩት መንግሥታት’ እውን ሆኗል፤ ግዴታችን ነው፡” እያለ የወጣቶቻችንን ሕሊና በተሸናፊነትና በተምበርካኪነት ፕሮፓጋንዳ በማደንዘዝ ሥራ ባይገባና በመሳሰሉ ሌሎች መጥፎ ንጥፈቶች እጁን ባያስገባ

የተከበሩ የወላጅ አባቱን ታሪክ አብሮ ባልተነሳ ነበር (‘ትሬንድ’ የሚሉት ነገር…)። ከኤርትራ ጋር ያልተወራረደ ሂሳብ እስካለን ድረስ ‘ስለ ኤርትራኖች’ እና ስለ ኤርትራ መሪ ስብዕና እና በጎ አሳቢነት ጥብቅና ቆሞ የጠላት ፕሮፓጋንዳ የሚያስተምር ሁሉ በባንዳነት ስለምናየው፤ ምሁራን ከዚህ ባሕሪ እንዲታቀቡ እንመክራለን። ከዚህ ሌላ ፤ ይቅርታ በመጠየቄም “የኢትዮጵያዊ ግሩም ሰው ምልክትነት ነህ” ብለው የምስጋና መልዕክት ለላኩልኝ ወንድም አብሬ አመሰግናለሁ።

## <u>*አሁን ወደ ዋና ርዕስ ልውሰዳችሁ።*</u>

‘አዲሱ የኢትዮጵያ መዝሙር’ ርዕስ የያዘ፤ በእጅጉ የማከብረው የስያትሉ ወዳጄ የብዙ መጽሐፍት ደራሲ ወጣቱ <u>**አማረ ቢሻው**</u> ወደ ስልክ መቀበያ መልእክት ልኮልኝ ነው ትናንት ማታ ያደመጥኩት። መዝሙሩን ከማድመጤ በፊት፤ የገመትኩት ይህ መዝሙር **የታማኝ በየነ** <u>‘ልዩ አንበሳ’</u> የሆነው፤ ግንቦት 7 እና ‘የኢሳያስ አፈወርቂ አፈቀላጤ” በሸዋ መንግሥታትና አማራ ላይ ‘ክፉ’ መጽሐፍ የጻፈ ‘ባንዳው’ አንዳርጋቸው ጽጌ ደርሶታል ተብሎ የሚነገርለት ጀሌዎቹ በየስብሰባው መድመቂያ “የሚያስደምጡን’ የሰለችን የአንዳርጋቸው መዝሙር መስሎኝ ነበር፡ ሆኖም ሳደምጠው ሌላ አዲስ መዝሙር ነው። ወዳጄ አማረን አመሰግናሉ።

## <u>*ስለ መዝሙሩ ትቼቴም እነሆ፤*</u>

ለወደፊቱ ብሔራዊ መዝሙር ሆኖ ተቀባይነት ካገኘ፤ መዝሙሩ አጠር ቢል {ለመሪዎች አቀባበል ሲደረግ “ትንሽ’ ረዘም የሚል ይመስለኛል፡ እንዲሁም በአንድ የስዕለ ድምፁ /ቪዲዮው/ ክፍል ብቻ የነገሥታቱ አቀማመጥ ቅደም ተከተል ሲያሳይ ከዮሐንስ ይልቅ ‘የጦር አዛዣቸውን’ ‘አሉላን’ ማስገባቱ ላይ ትንሽ የተሳሳተ ነው የሚል ካልሆነ በስተቀር፡- ወያኔ “ዜግነትን፤ የግለሰብን መብት የሚጻረር፤ ከጣሊያን ፕሮፓጋንዳ ቅጂ የተቀዳ ‘ብሔር፤ብሔረሰብ ሕዝቦች’ የሚለው <u>ትርጉም የለሽ</u> <u>ቡዱናዊና ማርክሳዊ</u> የሆነ የወያኔ መዝሙርና ሰንደቃላማን በእጅጉ ማጋለጥ የሚችል የሚደነቅ ስራ ነው። ከኔ የተሻለ እውቀት ባላቸው ተቺዎች እስኪመረመር ድረስ ፡ በኔ ግምገማ “ግሩም (beautiful, eye-catching-breath taking - spectacular) የሆነ የታሪክ እና የሰንደቃላማ ማራኪ ቅንብር ነው”።

ብዙ ሰዎች፤ ወያኔዎች የኢትዮጵያን ሰንደቃላማ ከጣሊያኖች ባንዴራ ጋር እኩል ነው የሚያይዋት ብየ ስናገር፤ አልዋጥ እንሚላቸው ታዝባለሁ። ጥልቅ ግንዛቤ

እንደሌላቸው ስለማውቅ እንዲህ ያሉ ሰዎች ሲገጥሙኝ፤ በትዕግስት ለማስረዳት ስሞክር እራሳቸው የሰንደቃላማ ምንነትና ክቡርነት ግንዛቤ የሌላቸው ከመሆናቸው ባሻገር"፡ ሰንደቃለማ በየወቅቱ የሚቀያየር ስለሆነ፤ ቢቀየር ባይቀየር ትርጉም የለውም" እስከማለት የሚደርስ ድምዳሜ ሳደምጥ፤ የማስረዳት ፍላጎቴ ስለሚቆም ራሳቸውን ከውስጥ ማየት ከማይችሉ ጋር ሃሳብ መለዋወጥ ስለሚያስቸግር፤ ከሚገርመኝ አንዱ ነገር ይኼ ነው።

አዎ፤ ወያኔዎች ኢትዮጵያን እና የኢትዮጵያን ሰንደቃላማ ይጠላሉ? አዎ!! ከመለስ ዜናዊ ጀምሮ እስከ ደራሲያኖቻቸው እና ጀሌዎቻቸው ድረስ በብዙ መንገዶች ሳያፍሩ፤ሳይሸማቀቁ፤ ታሪክን ሳይፈሩ ነግረውናል። መጽሐፍም ጽፈዋል። መለስ ዜናዊ ስለ ሰንደቃላማችን ጨርቅነት እና ጥላቻውም "ከሰንደቃላማው ጀርባው ካለው ጋር" መሆኑን ነግሮናል። ጥላቻውንም ግልጽ ለማድረግ "ከሰንደቃላማው ጀርባ" የሚላቸው "ኢትዮጵያ" "አማራ" እና "ኦርቶዶክስ ክረስትያን" ናቸው። በሽግግሩ ወቅት፤ በኢትዮጵያን አገር ወዳዶች እና በመለስ ዜናዊ የተሰባሰቡ አክራሪ <u>አስላማዊ ሃይሎች፤ጎሳዊ፤ማርክሳዊ እና በአክራሪ ተገንጣይ ቡድኖች</u> መሃል የነበረ የከረረ ንትርክ ታሪክ የሚያስታውሰው ነው።

ወያኔ እና መሪያቸው፤ ከጥላቻው የተነሳ፤ አማራን በሚሊዮኖች እንዲጠፉ አድርጓል፤ ቤተክርስትያኒቷን ለማፍረስ የራሱን ሰላዮች በማስገባት ገዳማትን አራክሷል። ቀሳውሰትን መነኮሳትን ረሽኗል። መነኮሳትና የትግሬ ቀሳውስት በኮሚኒሰት መፈክር ተጠምቀው ጠመንጃ ይዘው ***'ኢትቅተል'*** የሚለው መመሪያ ጥሰው ***'ንብስ'*** እንዲገድሉ አሰልጥኖ ታጋዮች አድርጎአቸዋል። ገዳማትን ዘርፏል። <u>**ሁለት ጊዜ**</u> ኢትዮጵያ ለ26 አመት በተከታታይ <u>**በትግሬ ፓፓሶች**</u> እንድትመራ አድረጓል። የአማራ መደበቂያ ነች እና አከርካሪዋን ሰብረናታል ብለው ነግረውናል። የክረስትያኖችን ማተብ አንገታቸው ላይ እንዳያስሩ እንዲበጠስ ትዕዛዝ እናስተላልፋለን ብለውናል። የቤተክርስትያኒቷ ጠላት የሆነው መለስ ዜናዊ ሲሞት በቀብሩ ስርዐተ ክንዋኔ ወቅት በቅድስት ሥላሴ ቤተክረስትያን ፊት ለፊት የመላእክቶቹን ምስል በመተካት፤ እንደ እየሱስ ክርስቶስ የመለስ ዜናዊ ፎቶግራፍ በትልቁ-ግራ-እናቀኝ-እንዲለጠፍ-ተደርጓል።



ኢትዮጵያን ገንጥሎ ያለ ባሕር ወደብ አስቀርቶ ለከባድ የሴክዩሪቱ/የአገራዊ ደህንነት/ ጥቃትና ፍራቻ ዳርጎናል፤ ዓረቦች ከብበውናል፤መቼውኑም ከማይተኙልን የሃይማኖትም ሆነ የድምበር ጸብ ካለን ከእስላማዊ አገር ጎሮቤቶች ሥር ወድቀን በወደቦቻቸው ክራይ እንድንከራይ አድርጐናል፡ደህንነታችን በነዚህ አገሮች ሥር ምሕረት እንዲወደቅ ሆኗል። ስለሆነም በራሰቸው በትግሬዎች ምሁራን ጥናት 82% የትግራይ ሕዝብ፤ አማራን በተለይ የሸዋ አማራን የሚጠሉ የወያኔ አድናቂዎች https://youtu.be/kZPFwIbs3WQ የወያኔን የጥላቻ ሴራ ተቀብሎ የወያኔን ባንዴራ በመልበስ በጭፈራውና ሰርግ ቤቱ፤ እንዲሁም በሰላማዊ ስብሰባ ጥሪዎችና አደባባዮች፤ በወያኔ ባንዴራ እያሸበረቁ **ራስን አጋንኖ የመስቀል ማንነት፤** የፖለቲካ ድርጅት **የመለያ ምልክት** አንደ **ብሔራዊ ሰንደቃላማ** አድርጎ በመተካት የሚነግሩን የምስጢሮች ምን ይሆን? የሚለውን እና ለምን የኢትዮጵያን ሰንደቃላማ እንደጠላትነት ለማየት ወሰኑ? የሚለው ለማየት ከጥቂቶቹ አንዱ በመጽሐፍ መልክ ከታተመው ማስረጃ ልስጠችሁ እና ልሰናበት።

የሚከተለው ጥቅስ ከትግርኛ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ የቀረበው ለወደፊቱ ከሚታተም መጽሐፌ ከሚከተለው ንውስ ምዕራፍ የተቀነጨበ ጥቅስ ነው።

አስደንጋጩ መጽሐፍ!

ቀዳማይ ወያነ ደራሲ የማነ ገብረመስቀል 2005 ዓ.ም በገጽ 71 -72 እንዲህ ይላል በትግርኛ (ትርጉም የራሴ-ጌታቸው ረዳ)

“ የትግራይ ሕዝብ (ከጣሊያን በኋላ) ያገኘው **‘ነፃነት’** ብለን የምንጠራው **‘ተገኘ የተባለው ‘ነፃነት’** በነጭ የባዕድ ወታደሮች ሲገዛ ቆይቶ፤ ባዕድ የሆነ አገረዊ በቀል በሆነ **ጥቁር (አበሻ) ወታደር መገዛት በመቻሉ ብቻ ነው**። ልዩነቱ **ያ ነጭ ነው**፤ ያ ደግሞ **ጥቁር ነው**። ልዩነቱ የቀለም ብቻ እንጂ፤ ***ሁለቱም ለትግራይ ሕዝብ*** **ባዕድ የሆኑ ወራሪዎች ናቸው**። በሌላ አነጋገር ባእድ የሆነው የፋሺስቱ ጣሊያን ቀጠልያ (አረንጓዴ) ነጭ፤ቀይ ቀለም ባንዴራ ከተሰቀለችበት ወርዳ በ ‘ቀጠልያ፤ቢጫ እና ቀይ’ ቀለም’ እማሃሏ ዘውድ የደፋ የይሁዳ አንበሳ ምልክት የላት ባንዴራ የተተካች በመሆኑ ብቻ ነው፤የሁለቱ ልዩነቶች። እሷም ቢሆን የሸዋ ገዢ መደቦች ከፈጣሪ የተሰጠቻቸው ሰማያዊ ፀጋቸው እንጂ ለእኩልነት ለኢትዮጵያ ሉአላዊነት ብሄር፤ብሄረሰቦች የማትወክል **ለትግራይ ህዝብ ምኑም ያልሆነች “የገዢዎቻችን /የወራሪዎች/ ባንዴራ ነች”።** *ምንጭ (ቀዳማይ ወያነ ደራሲ የማነ ገብረመስቀል 2005 ዓ.ም በገጽ 71 -72)*

## (3) *ዳግማይ ወያኔ!!!!!!*

“....ይህንን ሁሉ በማጠቃለል ወደ ሦስተኛ ምዕራፍ የተሸጋገረው የአንደኛ እና የሁለተኛ አማራ እና ትግሬ ስሜት ትግል (ፌዝ/ደረጃ)፦ ስንመለከት ዳ’ግማይ ወያነ’ ን ወለደ።በ 1967 ዓ.ም በማመጽ ወደ በረሃ ገብቶ ይህንን ይዞ ብቅ አለ፦ ” ። ይላል የማነ ገብረመስቀል።

## *የወያኔ ማኒፌስቶስ ምን ይላሉ?*

በ1968 (የካቲት 18) የታተመ መጸሔታቸው ደግሞ በግልጽ እንደተቀመጠው አጠቃላይ የህወሀት አላማ እና መድረሻ **“የጨቋኟ አማራ ብሄርን”** ጭቆና ለማስወገድ እና ከዚያም **“የትግራይ ሪፓብሊክ ማቋቋም ነው።”** “ **ህዝቡ (የትግራይ ሕዝብ) በኢትዮጵያዊነቱ አያምንም በሃይል ተይዞ ለዘመናት በአንድነት የቆየ ነው። ስለሆነም አሁን ባለው የህብረት መልክ ትግል ማካሄድ ‘ምኞትና የትምክህተኞች ሕልም ነው።** (መግለጫ ት.ህ.ነ.አ.ድ የመጀመሪያ እትም ገጽXI) (የወያኔ ገበና መህደር 2004 (እንደ ግሪጎርያን ዘመን አቆጣጠር ገጽ 25 (ጌታቸው ረዳ)

ጨቋኘዋ ብሔር (አማራ) የ3 ሺሕ አመት የሚያኰራ ታሪካችነን መመኪያቸውና መኩሪያቸው ሆኖ ይገኛል። ስለዚህም የሰረቀቺውን የትግራይ ታሪክ ለባለቤቱ ለትግራይ ብሔር እስካልመለሰች ድረስ **<u>ሰላም አታገኝም፤</u>** እንታገላታለን።" (ምንጭ እንደላይኛው) ።

ዛሬ ትግሬዎች 'መቐለ' እንጂ 'መቀሌ' 'ትግራይ' እንጂ 'ትግሬ' መባል የለበትም ይህ አማራዎች የፈለሰፉት ነው እያሉ (ትርጉሙ እንኳ ሳያውቁት፤ቤጃዎች የሰጡንን ቋንቋና ስያሜ በመርሳት(?) እየቀባጠሩ ወጣቱን ትውልድ ሲያሳስቱ፡- (ትግሬ የሚል ስም የትግሬ ቤተክርስትያናት እና መጻሕፍት ሳይቀሩ 'ትግሬ' እንጂ 'ትግራይ' የሚል በብዛት እንደማይዘወተር (በ1838 ምኒሊክ ባልነበረበት፤ ሃይሌ ባልነበረበት ዘመን የዓድዋ ቅዱስ ገብርኤል ቤ/ክርስትያን ገበዞች/አስተዳዳሪዎች/ ሳይቀሩ <u>*"....ዘቅዱስ ገብርኤል ኣድዋ ዘትግሬ"*</u>(Correspondence and Treaties 1800-1854 Edited by Sven Rubenson p.38 ) እያሉ ደብዳቤ ሲጻጻፉና ሲፈርሙ የነበረውን በመደበቅ፡ ሁሉም ወደ አማራ እየወረወሩ የአማራ ጥላቻቸውን እና ብሔራዊ ሰንደቃላማችንን ማንኳሰስ እና ማጥላላት የወያኔ ትግሬዎች ፋሽስታዊ ጸረ ሰንደቃላማችን የሚያደርጉት ቅስቀሳ ሁሉ 'የኢትዮጵያ አርበኞቻችን፤ ደራሲያን፤ ዘማሪያን፤ ገጣሚያን፤ ተዋንያን፤ ሰዓሊያን፤ጸሃፊዎች እና ሰብአዊ መብት ጠበቃዎች... ሁሉ ባላቸው እውቀት መታገል ወቅቱ የሚጠይቀው አስቸጋሪ የሕሊና ጦርነት ስለሆነ ባለቸው አቅም ሁሉ አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው።

ስለሆነም፤ የድርጅት መዝሙር ሳይሆን 'በቁጭት' ተነሳስተው፤ አሁን እንደወጣው ዓይነት አዳዲስ ኢትዮጵጵያዊ ብሔራዊ መዝሙሮች መውጣታቸው የሚበረታታ እርምጃ ነው።ለእንደዚህ ያለ ብዙ ጥረት የጠየቀ ኢትዮጵያዊነትን የሚያጎላ መዝሙር አቀነባብሮ ላወጡልን ዜጎች ከዚህ ደራሲ ልዩ ምስጋና ይድረሳችሁ እያለኩ ለዚህ ሰሞን ትችቴ አበቃሁ። https://youtu.be/lNBwG5msbYK

አመሰግናለሁ

ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ) Getachew Reda Ethio Semay getachre@aol.com